# ሃምሌ በፈረንሣይ፡ ግንቦት በኢትዮጵያ፡

## ከማተቤ፡ መለሰ፡ ተሰማ፡

ከዔምፓየር፡ ምስረታ በኋላ የቡርቦ፡ ሥርዎ መንግሥት፡ በፈረንሣይ ምድር፡ ተመልሦ ተንሣዔ ማግኜት የቻለው ፡ሕዝቡ በመጀመሪያ፡ ከሚራቦ ቀጥሎም ከሮቤክስ ፒየር፡ በመጨረሻም፡ ከናፖሊወን ጋር ከፍተኛ ለውጥ ካካሄደ፡ በኋላ፡ አብዩትና ጦርነት፡ በቃኝ በማለት፡ ናፖሊዩንን ከሥልጣን አውርዶ፡ ንጉሣዊዩን የቡርቦን፡ ሥርዎ መንግሥት፡ ቢተካውም ያ መንግሥት፡ ከ 1814 እስከ 1830 ለ16 ዓመት ሥልጣን ላይ በቆየበት፡ ወቅት የሾመው የፈረንሣይ ሕዝብ፡ መልሦ፡ ሊያወርደው እንደሚችል፡ በአለማሰብ፡ እንደ እኛውቹ  ጉዶች፡ ከሥራት ውጭ መሆንን ሲያያዘው፡ የሀምሌ እንቅሥቃሴ፡ የተባለ አዲሥ ንቅናቄ ተፈጥሮ፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ፡ ከሥልጣን እንደነቀለው፡ የሐገሬቷ ታሪክ ድርሣናት ይነግሩናል። በኢትዮጵያም፡ ሕዝቡ አብዩትና ጦርነት ሥለአሰለቸው፡ ከልብ ባይሆንም፡ መቸም ከደርግ የከፋ አይመጣም በሚል፡ የተሣሣተ ግምት፡ ይህንን የጥፋት መልከተኞች፡ ስብሥብ የወያኔ፡ መንጋ ፡በወርሃ ግንቦት ጥርጣሬ ባልተለየው፡ዝምታ በመቀበሉ፡ እንሆ ዛሬ እነዚህ፡ መጭውን ጊዜ የሚያዩበት፡ አይነህሌናቸው የታወረና፡ ለዘመኑ ሥልጣኔ ባይታውራንና፡ በፍጹም ቅናትና ምቀኝነት ለተበከለ፡ አእምሮ ባለቤት የሆኑት፡ ኋላቀር፣ ጠባብና ዘረኛ፡ ገዥዎቻችን፡ የኢትዮጵያን ህዝብ፡ በጋራ ሐገሩና በብሔራዊ ችግሩ፡ ላይ መክሮና ዘክሮ ዘላቂ መፍትሔ፡ እንዳይሻ፡ በዘር፣ በሀይማኖት፣ በቋንቋ፡ በመከፋፈል፡ አናጥለውና፡ የአንድነት፡ መንፈሱን፡ በጅጉ አዳክመው፡ እርስ በእርስ፡ ከማፋጀታቸውም በላይ፡ እነሱም፡ በቀጥታ፡የፈለጉትን በመግደል፣ በማሰርና በማሰደድ፡ ቀሬውን ደግሞ የሥራት ውጤት እንጅ፡ የዘር ዕዳ ባልሆነው፡ ህሌናን በሚያቆሥለው፣ አንደበተን በሚያሥረው፡ የድህነት አረንቋ ውሥጥ ዘፍቀው፡ የሰው ልጅ ሥጋው በሥጋትና በርሀብ፣ በእርዛት ውሃ ውሥጥ እንደገባ ጨው ሟሙቶ፡ እንዲያልቅ፡ እና ሀገሪቷም የእሮሮ፣ የሥቃይ፣ የፍርሃትና የጭንቀት፡ ድምጾች ያለማቋረጥ፡ የሚጮሁባት፡ ምድራዊ ሲወል እንደትሆን በማድረጋቸውና፡ የኢትዮጵያን ህዝብ፡ ትግሥት እንደፍርሀት፡ በመቁጠር፣ ሃያልነቱን በመናቅና በመደቅደቅ፡ ፊት መኖሪያና መከበሬያ፡ ሲሞትም መቀበሪያ፡ ሃገር እንዳይኖረው፡ ለም መሬቱን በአራቱም ማዕዘን እየቆረጡ፡ ለአጎራባች ሀገራት፡ በማደል ወ.ዘ. ተ. እንደህጻን፡ አፍንጫውን ሰንገው ከእሪት ሺህ ጊዜ እጥፍ የመረረ፡ የመከራ ህይወት መጋቱን፡ በመቀጠላቸው፡ እንደፈረንሣዩ ሀምሌ ንቅናቄ ሁሉ፡ በኢትዩጵያም፡ ከብሦት ማህጸን ተፈልቅቆ የወጣው፡ የግንቦት 7 የፍትህ፣ የነጻነትና የዲሞክራሴ ንቅናቄ፡ ግፉ ባንገፈገፋቸው፡ የሀገር ልጆች ተመሥርቶ አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እያሥመዘገበው ያለውን ውጤትና፡ በጥፋት መልዕክተኛው፡ ጎራም ያሥከተለውን፡ ክፍተኛ መደናግጥ፡ ሥንመለከት፡ እንደፈረንሣዩ ሀምሌ፡ የእኛው ግንቦት 7 ንቅናቄም ወያኔን በአጭር ጊዜ እንደሚነቅልልን የማያጠራጥር ሀቅ እየሆነ ነው።  ህሌናን፡ ያህል፡ ንጹህ፡ ሃብት፡ የተገፈፉትንና፣ በመንፈስ፡ የታወሩ፣ በምኞት፡ የሰከሩትን፡ ከእውነትና፡ ከእውቀት፣ እንዲሁም፡ ከኢትዩጵያዊነት፡ ጋር፡ በእጅጉ፡ ሆድና፡ ጀርባ፡ የሆኑ፡ የወያኔ፡ ቡድን፡ አባላትና፡ ሥብናቸውን፡ ለሆዳቸው፡ ታሪካቸውን፡ ለጥቅማቸው፡ የሸጡትን፡ የደቀ፡ መዛሙርቶቻቸውን፡ በአጭር ጊዜ እንቅስቃሴው ቀን ረፍት ሌት እንቅልፍ ያሣጣቸው ግንቦት 7 ውሎ ሲያድርና በድርጅታዊ ሥራው ሲዳብር ወያኔ መመከት አይደለም፡ ለደቂቃም እንኳን፡ ከፊቱ ሊቆም እንደማይችል፡ መገመት ከባድ አይመሥለኝም። ምክናያቱም፡ የሕዝቡ፡ ያጣው መሪ ድርጅት እንጅ፡ ብሦቱ፡ ገንፍሎ ገደቡን ያለፈበት ወቅት ላይ ለመድረሱ፡ ብዙ ምልክቶች እየታዩ ሲሆን ለአብነት ባለፈው ሰሞን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሥ፡ ተዋህዶ፡ሐይማኖት፡ ሲኖዶስ፡ በወያኔው ካድሪ በጳጳሥ ተብየው ላይ የወሰደው፡ እርምጃ የህዝብን መነሣሣት የሚጠቁም ነውና። እዚህላይ ግን አንዳንድ ወገኖቸ፡ ሐይማኖትን፡ ከኢትዮጵያውይነትና፡ ከፖለቲካ፡ ለይተን ማየት፡ አለብን፡ የሚል፡ ጎሣብ፡ በማራመድ፡ የዛሬ

አመት፡ አካባቢ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር፡ ትዘረጋለች፡ በሚል እርዕስ፡ አቅርቤው በነበረው ጽሁፍ መነሻነት፡ አስተያይታቸውን፡ ሰንዝረውልኝ ስለነበር፡ አሁንም የአባ ጳውሎሥን፡ የሥልጣን፡ ዕቀባ፡ ፋይዳ አሣንሰው፡ የሚያዩ ሊኖሩ እንደሚችሉ እገምታለሁ። በበኩሌ ግን፡ በሃይማኖቱም፡ ይሁን፡ በፖለቲካው፡ የመጠቀ፡ ዕውቀት፡ ኖሮኝ፡ የጠለቀ፡ ትንታኔ፡ በመሰጠት፡ አሣምናለሁ ብየም፡ ባይሆን፡ በሀገራችን፡ የሀይማኖትንና፡ የፖለቲካውን፡ ቁርኝት፡ በተመለከተ፡ በዚህ አጋጣሚ ምክናያታዊ፡ ሆኜ፡ ትንሽ፡ ለማብራራት፡ ልሞክር፡ ሐይማኖት፡ ከፖለቲካ መለየት፡ አለበት ወይንም የተለየ፡ ነው ለሚሉት ማሥገንዘቢያ ቢሆን።

ኢትዮጵያ፡ መናፍቃን፡ ጳጳሣት፡ ካሃዲያን፡ መኳንንት፡ በተሰገሰጉበት፡ ለክፋቱ፡ ጠንፍ፡ የሌለው፡ ተንኮልና፡ ምቀኝነቱን፡ አጥናፍ፡ በማይወሥነው፡ በወያኔው፡ ቡድን፡ መዳፍ፡ ሥር በመግባት፡ ያለ እርህራሄ፡ እንዲህ ታሽታ፡ ከመድቀቋ፡ በፊት፡ ምድር፡ ላይ፡ በጉልህ፡ እየታየ፡ በታሪክ፡ እየተዘከረ፡ ያለፈው፡ እውነታ፡ በማያሻማ፡ ሁኔታ፡ የሚያርጋግጠው፡ ኢትዮጵያዊነትና፡ ሀይማኖት፡ ደምና፡ ሥጋ፡ መሆናቸውን፡ ነበር፡፡ ደም ያለሥጋ፡ ሥጋ ያለደም፡ ህይወት፡ መዝራት፡ እንደማይችሉ፡ ሁሉ፡ ኢትዮጵያዊነትና፡ ሀይማኖትም፡ የማይነጣጠሉ፡ እንደነበሩ፡ግልጽ ነው፡ ይህንን፡ አባባሌን፡ ለማሥረገጥ፡ በሃሣብ፡ እርቄ፡ በመሄድ፡ ምንጭ፡ ማፈላለግና፡ በዋቢ፡ ማሥደገፍ፡ ሣያሥፈልግ፡ ከቅርቡ፡ ተነሥቶ፡ በአጭሩ፡ ጭብጥ፡ ለማሥያዝ፡ ያህል፡ የኢትዮጵያን፡ ብሄራዊ፡ አንድነት፡ ለመበታተን፣ የህዝቧን፡ ሰላምና፡ ነፃነት፡ ለማናጋት፡ የሚሞክረውን፡ ሁሉ፡ የውጭ፡ ወራሪና፡ ተስፋፊ፡ ሀይል፡ ለመመከት፡ የነበሩ፡ መሬዎች፡ ህዝባቸውን፡ በህብረት፡ እንዲነሣ፡ የሚቀሰቅሱበት፡ ትልቁ፡ መሣሬያ፡ ሃይማኖት፡ እንደነበር፡ የአድዋን፡ ጦርነት፡ የክተት፡ ጥሬ ብቻ፡ ማስታወሱ፡ በቂ ይመስለኛል። ከዚህ አኳያ፡ ማናችንም ብንሆን፡ ዛሬ፡ ሐገራችን፡ ሥቃይ፡ ተዘርቶ፡ መከራ፡ የሚበቅልባት፡ ምሪትና ዋይታ፡ የሚታጭድባት፣ በሽታ፣ እርሃብና፡ እርዛት፣ ሞት፡ በገፍ፡ የሚመረቱባት፡ የዜጎች፡ ሥብና፡ እየበሰበሰ፡ ማንነታቸው፡ ሰርዶ እየለበሰ፡ ያለባት፡ መሆኗንም፡ ሆነ በሁለንተናዊ፡ መልኩ፡ የደርሰባትን፡ ውርደትና፡ ውድቀት፡ እንዲሁም፡ በወያኔ፡ የበቀል፡ አሥተዳድር፡ እየተፈጸመ፡ ያለውን፡ መግለጫ፡ ቃላት፡ መለኪያ፡ መሥፈርት፡ የማይግኝለት፡ ዘግናኝ፣ አሣዛኝና፣ አሰቃቂ፡ ሁኔታ፡ ለመናገር፡ በተነሣን፡ ቁጥር፡ ከአለፈው፡ ሰፊ፡ የታሪካችን፡ ዕውቅያኖስ፡ ላይ፡ በመጠነ፡ ህሌና፡ ጨልፈን፡ ለመንደርደሬያነት፡ ማቅረብ፡ የግድ፡ ሥለሚልና፡ ሀቅም፡ ስለሆነ፡ የኢትዮጵያን፡ ታሪክ፡ ከሀይማኖት፣ ሀይማኖትን፡ ከፖለቲካ ጋር፡ ማገናኜታችን፡ ሥለማይቀር፡ ፖለቲካዊ፡ አንደምታውም፡ በዚህ፡ ውሥጥ፡ መንጸባረቁ፡ ግዴታ፡ ይሆናል።

እናም፡ በኢትዮጵያ፡ ውሥጥ፡ የነበሩና፡ ያሉ፡ ሀይማኖቶች፡ ያከናወኑትን፡ በሙሉ፡ ለመዘርዘር፡ ሰፊ፡ ጥናታዊ፡ ዝግጅት፡ የሚሻ፡ በመሆኑ፡ ልለፈውና፡ ለአብነት፡ የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክሥ፡ ተዋህዶ፡ ሀይማኖትንና፡ ቀደምት፡ መሬዎቹን፡ ብቻ፡ ወስደን፡ ለማየት፡ ብንሞክር፡ ከበቂም፡ በላይ፡ መገንዘብ፡ የምንችል፡ ይመስለኛል። የኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ፡ ሀይማኖት፡ ኢትዮጵያውያን፡ በገንዘብ፡ የማይገዙትን፡ ወይንም፡ በገጸበረከት፡ የማይቸሩትን፡ ደፋርነትንና፡ ልበሙሉነትን፡ ተላብሰውና፡ በእናት፡ ሀገር፡ ፍቅር፡ ታንፅው፡ እንዲያድጉና፡ ለነፃነታቸው፡ ቀናይ፡ ለሀገርና ለህዝባቸው ታማኝ ሆነው፡ እራሣቸው፡ ነድደው፡ ለሌላው፡ ብርሀን፡ በመስጠት፡ አርያነትን፡ እንዲካኑ፡ ከማስተማር፡ ጀምሮ፡ ሀገር፡ ሲወረር፡ ድንበር ሲደፈርና፡ ነገስታቱ፡ ክተት፡ ሰራዊት፡ ምታ፡ ነጋርት፡ ሲሉ፡

ካህናትና፡ ሊቃውንት፡ ታቦተ ህጋቸውን፡ የዘው፡ በመዝምት፡ የተጫወቱት፡ ሚናእና፡ የከፈሉት፡ መሷዕትነት፡ በቀላል፡ የሚመዘን፡ አይደለም፡ ብቻ፡ ሣይሆን፡ በቀጥታ፡ ፖለቲካም፡ ነበር፡ ማለት፡ ይቻላል፡፡ በሀይማኖቱ፡ መሬዎች፡ በኩልም፡ ለማየት፡ የረጅም፡ ጊዜውን፡ ትተን፡ ከትናንቱ፡ ብንነሣ፡ 1928.ዓ.ም.ፋሽስት፡ ኢጣልያ፡ ኢትዮጵያን፡ በወረረች፡ ጊዜ፡ ለእናት ሃገር፡ ክብርና፡ ለወገን፡ ነፃነት፡ ሲሉ፡ 1875.ዓ.ም በወቅቱ፡ አጠራር፡ በሸዋ፡ ጠቅላይ፡ግዛት፡ ሰላሌ፡ ፍቼ፡ ከተማ፡ የተወለዱት፡ የሃይማኖት፡ አባት፡ ብፁዕ፡ አቡነ፡ ጴጥሮስ፡ ሀምሌ፡ 22 ቀን፡ 1928.ዓ.ም አዲስ፡ አበባ፡ ላይ፡ በጎንድር፡ ጠቅላይ፡ ግዛት፡ በአፈረዋናት፡ ምክትል፡ ልጫ መስቅለ፡ ክርስቶስ፡ ከተባለ፡ ሰበካ፡ የተወለዱት፡ ብፁዕ፡ አቡነ፡ ሚካኤል፡ ህዳር፡ 24 ቀን፡ 1929.ዓ.ም ጎሬ ላይና፡ ሌሎችም፡ የዘርፉ፡ ሊቃውንትና፡ ካህናት፡ በእየቦታው፡ ማህበረሰቡን፡ ለመታደግ፡ ሲታገሉ፡ በኢጣልያን፡ ጦር ጭዳ ሆነዋል፡ ይህ ሁሉ፡ ለእኔ፡ የሀገራችንን፡ ፖለቲካ፡ ከሃይማኖት፡ ጋር፡ በማይለያይበት፡ ሁኔታ፡ ያስተሣሰረ፡ ጠንካራ፡ ሰንሰለት፡ ነው።

በአንድ፡በኩል፡ የዘርፉን ምሁራን፡ ሥራ ባልተሟላ፡ ሙያ እንዳልሻማ፡ በመሥጋት፡ በሌላ በኩል፡ ደግሞ ቁም ነገሩን፡ በአጭሩና፡ በቀላሉ፡ ለማሥረዳት፡ በጣም ውሱን፡ የሆኑ፡ ነጥቦችን፡ በምሣሌነት፡ ጠቃቀሥሁ፡ እንጅ ኢትዮጵያንና፡ ፖለቲካዋን፡ ከሀይማኖት፡ የሚያቆራኟት፡ በቀደምት፡ አባቶቻችን፡ የተፃፉ፡ ብዙ፡ ሀቀኛ ገድላት፡ አሉ፡ የዛሬን፡ አይድርገውና። አዎ!! ዛሬላይ ቆመን፡ ትናንትን፡ በአይነ ህሌናችን፡ ሥንቃኝ፡ ለ18 አመት፡ በሁሉም፡ ዘርፍ፡ ምንያህል፡ እንደካሮት፡ ቁልቁል፡ እንዳደግን፡ ስለምንረዳ፡ ያንገበግበናል፡፡ ይህ እንግዴህ፡እውነቱን፡ ለመናገር፡ የትናንት፡ ሀይማኖት፡ አባትና፡ መሬዎች፡ ለመላው፡ ህዝባቸው፡ ቤዛ ሲሆኑ፡ የዛሬው፡ ለአንድ፡ መንደር፡ ፖለቲካ፡ መሥለፋቸው፡ እንጅ፡ የኢትዮጵያ፡ ፖለቲካና፡ ሀይማኖት፡ የተለያዩበት፡ ጊዜ፡ ብዙም፡ አለመሆኑን፡ ያረጋግጥልናል።

ይቅርታ ውድ አንባብያን፡ ሥለ ሃይማኖትና ፖለቲካ፡ ብዙ አልሁ መሰል፡ አሁን ወደ ጽሁፌ ተግባራዊ ቅኝት፡ ልመለሥና፡ ያለንበት ወቅት፡ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የሞት ሽረት፡ ትግል የሚካሄድበት፡ ወሣኝ ምዕራፍ፡ መሆኑን የሚያሥገነዝቡ፡ ብዙ ምልክቶችን፡ እያየን ነው። እንደሚመሥለኝ፡ ቀሬው እየታገሉ ያሉ ኢትዮጵያውያንን፡ ቆምን መጠበቅ ሣይሆን፡ እያንዳንዳችን፡ ሀገሬ ከእኔ ምን ተጠብቃለች? ማድረግ ያለብኝሥ ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለእየራሣችን፡ በማቅረብ፡ ቁርጥ ያለ መልስ ማግኜትና፡ የትግሉን ጎራ ፈጥኖ በመቀላቀል፡ የፈረንሣይ፡ ህዝብ በሀምሌ፡ ንቅናቄ፡ መሬነት ከቡርቦ፡ ሥርዎ መንግሥት፡ ነፃ እንደወጣው፡ ሁሉ እኛም፡ በአንድነት፣ ለአንድነት፡ ቆመን፡ የሀገራችንን፡ የተንሣዔ ዕለት ማፋጠን፡ ነው።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

ሞት ለወያኔ!!!